# ከዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ለተሰጠ ማብራሪያ
# ከአቶ አባይነህ ብርሃኑ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የቀረበ ምላሽ

የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የፓርላማ ተመራጮች ጥቅምት 29 ቀን 2000 ዓ.ም የቅንጅት ፓርቲን ህጋዊነት አስመልክተው በሰጡት መግለጫ ለይ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም ኖቬምበር 15,2007 በድረ-ገጽ ላይ ማብራሪያ መስጠትዎ ይታወቃል። በማብራሪያዎ ውስጥ የሚከተሉት ሦሥት ፍሬ ሃሳቦች ይገኛሉ። እነሱም፦

1ኛ, የቅንጅት አመራር አባላት ከወህኒ እንደወጡ ፓርቲው ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ ለማድረግ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ፣ አቶ ብሩክ ከበደና እርስዎም ጭምር ያሉበት አንድ ኮሚቴ መቋቋሙንና ይህ ኮሚቴ ከአቶ ተመስገንና ከአቶ መሃመድ ጋር ስብሰባዎች አካሂዶ የእነ አቶ ተመስገን አመራር ከእስር ለተፈቱት የአመራር አባላት የፓርቲ ፈቃዱን ለማስረከብ ከስምምነት ላይ መድረሱን፣

2ኛ, ቀደም ሲል በላዕላይ ምክር ቤቱ የተቋቋመ ኮሚቴ እያለ ሌላ ኮሚቴ የማቋቋም አስፈላጊነት ግልጽ ያልሆነልዎት መሆኑን፣

3ኛ, አሁን የተቋቋመው የአስተባባሪ ኮሚቴ አባል አለመሆንዎንና አባል እንዲሆኑም የጠየቀዎ ማንም ሰው አለመኖሩን መግለጽዎ ናቸው።

የተከበሩ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም ፓርቲያችን ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ ለማድረግ ቀደም ሲል ጉዳዩን ሲከታተሉ የቆዩ መሆንዎ ይታወቃል። ጥቅምት 29፣2000ዓ.ም መግለጫ በሰጠው የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የፓርላማ ተመራጮች ኮሚቴ ውስጥ እንዲገቡ የተደረገውም ለጊዜው እርስዎ አገር ውስጥ የሌሉ ቢሆንም ወደ ኢትዮጵያ በሚመለሱ ጊዜ በሒደቱ ተሳትፈው ሥራዎን ቢቀጥሉ የሚጠቅም ተግባር ያከናውናሉ ብሎ ኮሚቴው ስላመነበት መሆኑን በቅድሚያ ልናሳውቅዎ እንወዳለን።

በአሁን ጊዜ ፓርላማ የገቡና ያልገቡ (የታሰሩ የአመራርን አባላትን ጨምሮ) ተመራጮችን የያዘ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋናው ምክንያት የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን ህጋዊ ሰውነት የማስገኘትን ጉዳይ ለማፋጠንና ፓርቲው ሥራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ለማስቻል ነው። ይህም ሲባል፦

1ኛ, የቀድሞው ኮሚቴ አባላት ሦሥቱም ወደ ውጭ ሃገር ሄደው እስካሁንም ባለመምጣቸው ከቅንጅት ተመራጮች ጋር በመገናኘት የፓርቲ ባለቤትነትን የማስመለሱን ተግባር የሚሰራ ባለመኖሩ ይህን ሃላፊነት ለማከናወን ስለታመነበት፣

2ኛ, የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ህልውና ለአደጋ ተጋልጦ አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከገጠመው የህልውና ማጣት ፈተና ለማውጣት የሚያስችል መፍትሔ ለመፈለግ፣

3ኛ, ቀደም ሲል በህገ ወጥ መንገድ ጊዜያዊ ፈቃድ የተሰጣቸው ግለሰቦች ለሁለት ተከፍለውና ተቧድነው ባንድ በኩል አቶ ተመስገን ዘውዴ የፓርቲው መሪ እኔ ነኝ በማለት የጀመሩትን የፍርድ ቤት ክርክር እንዲያቆሙና በሌላም በኩል አቶ አየለ ጫሚሶ ህዳር 1ቀን 2000 ዓ.ም ስብሰባ ለመጥራት መወሰናቸው ተገቢ አለመሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ተረድቶ እውቅና እንዳይሰጣቸው ለማስገንዘብና መሠል ተግባራትን ለማከናወን አስተባባሪ ኮሚቴው የተቋቋመ መሆኑን ለመግለጽ እንሻለን።

ቀደም ሲል የቅንጅት አመራር አባላት በእስር ቤት ስለነበሩ ፓርቲው ያስመረጣቸውን የፓርላማና የክልል አባላትን የሚያስተባብራቸው አካል እንዳልነበረ ይታወቃል። አሁን እኛ የአመራር አባላቱ ከእስር በመፈታታችንና ቢሯችንም በመከፈቱ የፓርላማና የክልል ተመራጮች በቅንጅቱ አስተባባሪነት

በጽህፈት ቤታችን እየተገኙ የፓርቲያችንን ህልውና ባፋጣኝ የማግኘት ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ተገቢ እርምጃ መሆኑ ይታመንበታል። እየተደረገ ያለውም ይኸው ነው። የተከበሩ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም በማብራሪያዎ ላይ እንደገለጹት እውነት እነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ፈቃዱን ለቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ለማስረከብ የተስማሙ ከሆነ ሌሎች የፓርላማ ተመራጮች በቅንጅት ጽህፈት ቤት ስለ ፓርቲው ህጋዊነት ሲመክሩ እነሱ ጥሪ ተደርጎላቸው በጉዳዩ ለመሳተፍ ለምን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ? ያስመረጣቸው የቅንጅት ፓርቲ ጽህፈት ቤት መምጣትንስ ለምን ሸሹት?

የተከበሩ ዶ/ር ያዕቆብ እንደሚሉት እነ አቶ መሃመድ አሊ እውነት ፈቃዱን ሊሰጡን የወደዱ ከሆነ ከእስር ለተፈቱት የአመራር አባላት ፈቃዱን አስረክቡ ያሏቸውን የፓርላማ ተመራጮች ለምን በጀርመን ድምጽ ሬድዮ ጣቢያ ሲያወግዙ ተደመጡ?

የቅንጅት አመራር አባላት ከእስር በተለቀቁበት ወቅት እነ አቶ ተመስገን ዘውዴ በ15 ቀን ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን እናስረክባለን ብለው የገቡትን ቃል በሦሥት ወር ጊዜ ውስጥም እንኳን ሊፈጽሙ አለመቻላቸውን የተከበሩ ዶ/ር ያዕቆብ እንዴት ተመለከቱት?


አባይነህ ብርሃኑ
የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል